# ደስ ያለው ይዘምር ወይስ ካሴት ያውጣ?

**ከጳውሎስ ፈቃዱ**

paulosvictory@yahoo.com

ከሁለት ዘማሪዎች ጋር ወደ አዋሳ እየሄድኩ ነው (በእናታችሁ ስማቸውን አትጠይቁኝ):: እዚያ ስንደርስ ሌላ ሦስተኛ ዘማሪ አገኘን:: ይህ ዘማሪ ከእኔ ጋር ካሉት ዘማሪዎች ለአንዱ የሚሆን መዝሙር አዘጋጅቷል:: ግጥሙን ካስጻፋቸው በኋላ ዜማውን ለማስለመድ ሲጀምረው ቁጭ ዘፈን ይመስላል:: አብረውኝ የነበሩት ዘማሪዎችም ይህንን ዐውቀዋል:: «ይህማ የእገሌን ዘፈን ይመስላል» አለ አንደኛው የዘፋኙን ስም ጠቅሶ:: ያኛውም ለማስተባበል አልሞከረም:: «አዎን፣ ከዚህኛው ዘፈኑ ላይ ነው የወሰድኩት» በማለት ዘፈኑን ማንጐራጐር ጀመረ:: ከእኔ ጋር ከሄዱት ዘማሪዎች አንዱ ቀጠል አድርጐ፣ «እኔም እኮ ከዚያኛው ዘፈኑ ላይ ወስጃለሁ» በማለት የሆነ መዝሙር በፉጨት አሰማን:: እኔ በድንጋጤ እንደ ጅብራ ከተገተርኩበት ስፍራ በዕፍረት ጉንዳን አክያለሁ፤ ሆኖም ከምንም አልቆጠሩኝም:: ዘማሪዎቻችን ግጥም፣ እነ ኤፍሬም ታምሩ ደግሞ ዜማ በመስጠት እንደሚያገለግሉን ግን ከዚያን ቀን ጀምሮ ማወቅ ችያለሁ::

ይህ ከሆነ ስድስት ዓመት አልፎታል:: እኔም ብዙዎቹን ዘማሪዎች በግል ለማናገርና ለመምከር ሞክሬያለሁ:: ግና ጥቂት የማይባሉ ዘማሪዎች ከዚህ ዓመላቸው ፈቀቅ ማለት አልሆነላቸውም:: አሁን አሁንማ በአንድ የመዝሙር ካሴት ላይ ሰባትና ስምንት የዘፈን ዜማዎችን ወደ መስማት «አድገናል»:: ለመገሠጽ ሲሞከርም፣ «በመዝሙሮቹ ተባርከንባቸዋል፤ ለምን ትነኳቸዋላችሁ?» በማለት የሚቆጡ ከያሉበት ብቅ ይላሉ:: የእነርሱን የ«ተባርኬያለሁ» ስሜት የትክክለኛነት መለኪያ ያደረገው ማነው? የአንድ ሰው ስም ከተጠቀሰም፣ «ያጠፋው እርሱ ብቻ አይደለም፤ ስለዚህ እርሱ ተለይቶ ለምን ይወቀሳል?» የሚል አመክኖያታዊነት የጐደለው ተቃውሞ ይደመጣል:: ኧረ ለመሆኑ ይህ ሁሉ ጥፋት ሲፈጸም የት ነበሩ? ምናልባት በእንቁላሉ ሥርቆት ጊዜ፣ ማጨብጨባቸውን አቁመው ቢገሥጿቸው ኖሮ ከብዙ ዕፍረት ባተረፉን ነበር!

ይህን ሁሉ የማቀርበው ግን ጠላቶቼን የማብዛትና እንጀራዬን የማጥፋት ሞኝነት ይዞኝ ወይም ብሽሽቅ አምሮኝ አይደለም:: ትውልዱን በማቅናት የባለአደራነት ድርሻዬን ለመወጣት በማሰብ ብቻ ነው::

ሆን ብለው ከዘፈን ዜማ የሚወስዱ ዘማሪዎችን ዐውቃለሁ:: ጥቂቶችንም አነጋግሬያለሁ:: «ዜማ ሁሉ የእግዚአብሔር ነው፤ ለሰይጣን ማን ሰጠው? ስለዚህ እንደ ፈለግን መውሰድ እንችላለን» ይላሉ:: በዚሁ ከቀጠሉ በዜማ ስርቆት ተከስሰው አንድ ቀን ፍርድ ቤት እንዳይቀርቡ እሰጋለሁ:: «የዘፈን ዜማ ስንጠቀም፣ የማያውቀውን መልእክት በሚያውቀው ዜማ ለሰይጣን እያቀረብንለት ነው» የሚሉም አሉ («ወደው አይሥቁ!» ይላል የአገሬ ሰው):: በእነርሱ ቤት፣ ሰይጣን እንደ ሕንድ ፊልም «የሌቦች አለቃ» መሆኑ ነው:: እንዲህ ከተቻለማ መዝሙር እንዲሆኑልን የምንፈልጋቸው ብዙ «ምርጥ ምርጥ» ዘፈኖች ስላሉ ከሆነ አይቀር አንደኛውኑ ጥቆማ ብንጀምር ይሻለናል:: እኔ በበኩሌ «የነገን ማወቅ ፈለግሁ» የሚለውን ዘፈን መርጫለሁ::

ዜማ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው እንዴ? ክርክሩ ውሃ አያነሣም:: ከቲአትር ቤትና ከዘፈኑ ዓለም አካባቢ የመጡ ሰዎችም ይህን አይነግሩንም:: አንዳንዶቹ የዘፈን ዜማዎች ጫት በመቃም፣ ሌሎቹ ደግሞ ሰይጣንን በመለማመን የሚደረሱ ናቸው:: በርካቶቹ ዘፋኞች ውሎአቸው ጠንቋይ ቤት እንደ ሆነ በቅርቡ በኢትዮጵያ የተለያዩ መገናኛ ብዙሃን ሲገለጽ ከነበረው የአንድ ጠንቋይ ገድል ተረድተናል:: ከዘፈን ደራሲዎች መካከል አንደኛው ሲጸለይለት በውስጡ የነበረው ርኩስ መንፈስ፣ «ዜማና ግጥም የምንሰጠው እኛ ነን» ይል ነበር:: «ሳብ በለው የሀሙሱን ፈረስ» የሚል ዘፈን አለ አይደል? «የሀሙሱ ፈረስ» ማን ይመስላችኋል? «የበረሀው ዐውሎ ነፋስ» የሚል ዘፈንም አለ:: ይሄስ ማነው?

ነውር የሚተላለፍባቸው አሳፋሪ ዘፈኖች ከመብዛታቸው የተነሣ፣ «‘በስምንተኛው ሺህ ዘፋኝ ይበዛል’ የሚል ንግርት አለ» እያሉ የሚያሾፉ የትምህርት ቤት ጓደኞች አሉኝ:: እውን ዜማ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነውን?

ለመሆኑ የዘፈን ዜማ ወደ መዋስ የደረሱት አዲስ ዜማ መፍጠር አቅቷቸው ነው ወይ? መጽሐፍ ቅዱስም ቢሆን፣ «ለእግዚአብሔር አዲስ ዝማሬ ዘምሩ» (መዝ. 96:1፣ 40:3 - አ.መ.ት) በማለት በግልጽ ይናገራል።

መንፈስ ቅዱስን የት አድርገነው ነው? ለሚጠሩት ሁሉ ባለጠጋ የሆነው እግዚአብሔር ብንጠይቀው በልግስና የማይሰጠን ይመስል ቅልውጥና ምን ወሰደን?!

በፊት የመዝሙር ዜማ የሚወስዱ ዘፋኞች ነበር የሚበዙት፤ ምክንያቱም መዝሙሮቻችን በዘፋኞች ዘንድ ተሰሚነት ነበራቸው። አሁን ደግሞ በዚያው መጠን የእነርሱ ዘፈን የእኛን ዘማሪዎች ቀልብ ሰርቋል። ይህም የእኛ ዘማሪዎች የዘፈንን ዜማ በመስረቅ መታማት እንዲጀምሩ አደረገ።

ዘፈን በመዝሙር ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ከልክ እያለፈ ነው። ቴዲ አፍሮ የተነሣውን ዐይነት ፎቶ ተነሥቶ ከእርሱ ጋር አንድ ዓይነት ፖስተር የሚያዘጋጅ ዘማሪ በቅርቡ አይተናል። በነገር ሁሉ እርሱን መምሰል የሚያምራቸው የእርሱ ደቀ መዛሙርት ከመካከላችን ብቅ ማለት ጀምረዋል። አኮራረጃቸው፣ ስም ሳይቀር እንደሚገለብጥ ቀሽም ኮራጅ ተማሪ ነው። አንዳንድ ዘፈኖች መሐል ዘፋኞች የማቃሰት ድምፅ መቀላቀል ይወዳሉ። መልእክቱ ሰዎችን ለአልጋ ላይ ጨዋታ ለማነሣሣት ወይም እዚያ ላይ ያሉ ለማስመሰል እንደሚደረግ እገምታለሁ። አስገራሚው ግን አንዳንድ መዝሙሮችም መሐል የሚያቃስቱ ዘማሪዎችን እየሰማን መሆኑ ነው። ምን ማለት እንደሆነ አስተውለውት ይሆን? እንደ ዘፈን፣ «የታለ እጃችሁ? እስቲ ሞቅ አድርጉት እባካችሁ?» የሚሉ ዘማሪዎችም አሉ።

ሆኖም ሁሉም ዘማሪዎች ይህን የሚያደርጉት ሆን ብለው ነው የሚል ጭፍን ግንዛቤ የለኝም። ሳያውቁ የሚሳሳቱም ይኖራሉ። የክልሎችን ሳይጨምር በአዲስ አበባ ከተማ ብቻ ወደ አራት አካባቢ ኤፍ ኤም ሬዲዮዎች ያሉ ይመስለኛል። ሁሉም ሲሞዝቁ ነው የሚውሉት። ስለዚህ ሰዎች ሻይ ሲጠጡና ታክሲ ሲጠቀሙ ወደዱም ጠሉ ዘፈን ሊሰሙ ይችላሉ። በዘፈን ስሜት ውስጥ ሆነው መዝሙር እንጻፍ ካሉ ደግሞ ይህ የተጠቀጠቀት ዜማ ደግሞ የመዝሙራቸው ዜማ ሆኖ ብቅ ይላል። መዝሙሩ ከዘፈን የተመሳሰለበትን አንድ ዘማሪ ይህንን ጽሑፍ ሳዘጋጅ አናግሬው ነበር። «በንዳዬ ሆኜ ከእግዚአብሔር የተቀበልኳቸው የመሰሉኝ መዝሙሮች ዜማቸው የዘፈን ዜማ ሆኖ እየተገኘ የተውኳቸው ብዙ ናቸው» ብሎኛል። መቼም የችግሩ ስፋት መጣጥፍ ሳይሆን መጽሐፍ ይወጣዋል!

አሁን አሁን ወደ ክልሎች እየወጡ ከአዲስ አበባ ርቀው ጠፍተው ይሆናል እንጂ «ቆርቆሮ ያለው (ያለሽ)» እያሉ የሚዞሩ ትጉ ሠራተኞች በየሰፈራችን አይጠፉም ነበር። የወዳደቁ ብረታ ብረቶች፣ አሮጌ ብልቃጥ፣ ዐፈር ውስጥ የተቀበረ የጫማ ሶል ሁሉ ሲያገኙ ይገዛሉ። እግዚአብሔር ግን እንዲህ አይደለም። ከየትም የተሰበሰበ ኮልኮሌና ቅራቅንቦ ዜማ ለእርሱ አይቀርብለትም።

የመልእክታቸው ተወራራሽነትማ አስደንጋጭ ነው። አንዱ ዘማሪ የሌላኛውን መዝሙር በሌላ ዜማ ለውሶ ያቀርብልናል። ስለዚህ አዲስ ነገር ከመፍጠር ይልቅ ፍራሽ አዳሽ ይመስል አሮጌውን መዝሙር ገረፍ ገረፍ አድርገው ለገበያ ያቀርቡታል። ከተለያዩ መዝሙሮች ተለጣጥፈው የተበጁ ድሪቶ መዝሙሮች በዝተዋልና አዲስ ፈጠራ እያማረን ከቀረ ቆየ።

«የሞት መልአክ አያስፈራኝም
ተሸሽጌያለሁ አያገኘኝም»። ይህን መዝሙር ታውቁታላችሁ? ዶ/ር ደረጀ ለልደታ መካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን የሰጠው ዝማሬ ነው። ካልተሣሣትኩ 20 ዓመት አርፎታል። ይህንን መዝሙር በቁጥር 4 ካሴቷ ላይ ምሕረት ኢተፋ የራሷ አስመስላ ቃል በቃል አቅርባዋለች፤

«የሞት መልአክ አያስፈራኝም
ተሸፍኛለሁ አያገኘኝም» በማለት። ልዩነቱ «ተሸሽጌያለሁ» የሚለው፣ በ«ተሸፍኛለሁ» መቀየሩ ብቻ ነው። ሌላ ልጨምርላችሁ። የጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን «ሀ» መዘምራን በቁጥር 1 ካሴታቸው ላይ

«ጌታ ቀድሞ ተኝቶበት
ስፍራውን ይዞ ዐርፎበት

እንዴት ይሰጥማል መርከቡ
ምንስ ቢያይል ወጀቡ?» ብለው ዘምረዋል፡፡ እርሷ ደግሞ ከዓመታት በኋላ፣
«ጌታ ኢየሱስ ተኝቶበት
ስፍራውን ሁሉ ተቆጣጥሮት
እንዴት ይሰምጣል መርከቡ
ምንስ ቢያይል ወጀቡ» በማለት የካሴት ዘመቻዋን አሐዱ ብላ ጀምራበታለች፡፡ አጋጣሚ ይሆንን? ካልሆነ የሰው የመዝሙር ደብተር ውስጥ ምን ልትሠራ ገባች?! አንድ ልጨምርበት

«ጅማሬዬ ላይ ቆሞ ፍጻሜዬን ያየ
ይኼ ነው አምላኬ ከሁሉ የተለየ (ሲሳይ አበበ #2 - 1998)
ጅማሬዬ ላይ ሆኖ ፍጻሜዬን ያየ
ይሄ ነው የኔ አባት ከሰው የተለየ» (ምሕረት ኢተፋ ልዩ ዕትም - 1998) አንድ የመጨረሻ ብቻ ታገሡኝ፤

«የአላዋቂዎች ልቦና በሰዎች ተስፋ ያደርጋል
ግን እግዚአብሔር ብቻ ደኅንነትን ያዘጋጃል፡፡» (መጋቢ ተስፋዬ ጋቢሶ #4 1984)
«ያለ አዋቂ ልቦና የሚታየውን ብቻ ያያል
ግን እግዚአብሔር ብቻ መድኃኒትን ያዘጋጃል፡፡» (ምሕረት ኢተፋ ልዩ ዕትም 1998)

«ምህረት ብቻ አይደለችም ይህንን ያደረገችው፤ የእርሷ ስም ብቻ ለምን ይጠቀሳል?» የሚለው የተለመደው ጥያቄ እንዳይነሣ አንድ ሁለት ጣል ላድርግበት፡፡
«የምድረ በዳው ዳዊት ና ውጣ
የዜማ ጊዜ መጣ፡፡
በእሥር ላይ ያለህ ዮሴፍ ና ውጣ
የክብር ዘመን መጣ» (ያሬድ ማሩ #1-1996)
ከሚቀጥለው ጋር አስተያዩት፡፡ በመካከላቸው የአራት ዓመታት ልዩነት አለ፡፡

«የምድረ በዳው ዳዊት ከጫካው ውጣ
የመንገሥ ዘመን መጣ
ባለ ራዕዩ ዮሴፍ ከግዞት ውጣ
የመክበር ዘመን መጣ» (ሰናይት እንግዳ #6 - 2000)፡፡
ሌላም ልጨምርላችሁ፤

«ማደሪያህ በምስጋና ይሞላ
አምላክ የለምና ካንተ ሌላ» (እንዳልካቸው ሐዋዝ #1 - 1992)
ይሄም "Copy Paste" ይመስላል

«ማደሪያህ በምስጋና ይሞላ
አምላክ የለምና ከአንተ ሌላ» (ኤልያስ ወልዴ #1 - 2000)፡፡

«ተራው የእኔ ነው የእኔ
አምላኬ አለና ከጎኔ» (ደስዬ ወልዴ #2 - 1997)፡፡ ይቺም በሌላኛው ላፍ ተደርጋለች፤

«ተራው የእኔ ነው የእኔ
ጌታም አለ ከጎኔ» ((ኤፍሬም ዓለሙ #1 - 1998፡፡

በእርግጥ በጣም የወደድነው፣ ጆሮአችንን የምንሰጠውና ልባችንን የነካ ነገር ውስጣችን ሊቀር፣ ከዚያም በራሳችን ሥራ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡ ስለዚህ ከዚህ በፊት የነበረ ነገር ሳይታወቅ በእኛ ሥራ ላይ ሊንጸባረቅ ይችላል፡፡ ግን ልክ አለው፡፡ ከዚህ በላይ

የዘረዘርናቸውን በሚመለከት፣ «እነዚህ ሁሉ በአጋጣሚ ነው የሆኑት» እንደማትሉ ተስፋ አደርጋለሁ:: የዚህ ዐይነት «ምንተፋዎች» ብዙ ናቸው:: ከተፋው ሳያንሰን ምንተፋው! ለናሙናነት እነዚህ ይበቁናል:: ካነሰ ሌላ ጊዜ እንጨምርበታለን:: አሁን የአሳብና የቃላት መወራረስን ላሳያችሁ::

«ሰበብ ፈላልጌ ምክንያት ፈላልጌ ላሞጋግስህ» (ኢ.አ አማኑኤል ኀብረት ቤተክርስቲያን #1-1996)::

«ምክንያት ፈልጌ ላመስግን እንጂ
ሰበብ ፈልጌ ልዘምር እንጂ» (ተከስተ ጌትነት #4 - 1996)::

«ምክንያት ሰበብ ፈላልጌ
ልሰዋለት ለአምላኬ» (ዳግማዊ ጥላሁን #2 - 1997)::

ሦስቱም በአንድ አእምሮ የታሰቡና በአንድ ምህዋር የሚዞሩ ፕላኔቶች ይመስላሉ:: ችግሩ የመመሳሰል ብቻ አይደለም:: ለመሆኑ እግዚአብሔርን ለማመስገን ሰበብ ፍለጋ ምን አንከራተታቸው?

ስንኞችን እየነጠልን ካየንማ ጉድ ነው:: አንዱ የተለየ ዘይቤ ሲያመጣ የቃላት ጠኔ ያለባቸው ሌሎች እንደ ሠልፈኛ ተከትለውት ይነጉዳሉ፤ የራሱ ነገር የሌለው ዘማሪ ለተከታይነት ራሱን ያዘጋጀ ነውና:: ለአብነትም የሚከተሉትን ማየት ይቻላል፤
«ከትላንቱ ዛሬ ሕይወቴ አምሮበታል
መርዶው ለዲያብሎስ ማለዳ ደርሶታል» (ደረጀ ከበደ #8 - 1988)::

«ከትላንቱ ዛሬ ሕይወቴ አምሮበታል
ለቅሶ ማታ ነበር ጠዋት ደስታ ሆኖአል» (ኤፍሬም ዓለሙ #2 - 2000)::

«መዝሙሮች ምንም መመሳሰል የለባቸውም» እያልኩ አይደለም:: በተለይ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ቃል በቃል የሚወስዱ ከሆነ ምንጩ አንድ ነውና መመሳሰሉ አይቀሬ ነው:: ይህንን እደግፋለሁ:: ስለዚህ ተመሳሳይ ቃላት አይጠቀሙ ለማለት አልደፍርም:: «እምቢ» በሚል ቃል ላይ የተመሠረቱ መዝሙሮችን በምሳሌነት ላቅርብ፤
«እምቢ አሻፈረኝ ለምስሉ አልሰግድም» (መጋቢ ተስፋዬ ጋቢሶ #1)::
«የእግዚአብሔር ነኝ እምቢ» (ደረጀ ሙላቱ #1)
«እምቢ ሙት መንፈሴ ነቃ» (አዜብ ኃይሉ #1):: ሦስቱም የየራሳቸው ውበትና ጠንካራ መልእክት ያላቸው የተለያዩ መዝሙሮች ናቸው:: ሁሉም እንዲህ ቢሆኑ በምን ዕድላችን? እንዳያያዛቸው ከሆነ ግን፣ አንዱን መዝሙር ከሰማን ሁሉንም እንደሰማን ይቆጠራል::

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ ግጥሞችም ሞልተውናል:: ሳሙኤል አክሊሉ የተባለው ዘማሪ የቁጥር 1 ካሴቱ ርዕስ «የእኔ ሰረገላ» ይባላል:: ብዙዎች በሰረገላቸውና በፈረሳቸው ሲታመኑ እርሱ ግን በእግዚአብሔር ላይ መታመኑን መግለጽ የፈለገ ይመስላል:: የተነሣበት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍልም፣ መዝሙረ ዳዊት 20:7 እንደሆነ አስባለሁ:: ሆኖም የገለጻ ችግር አለበት፣ «የእኔ ሰረገላ ፈረሴም እርሱ ነው» በማለት ኢየሱስን ገልጾታል:: ጌታ ኢየሱስን በዚህ መልኩ ለመግለጽ መድፈሩ ያስደነግጣል:: እንኳን ኢየሱስ የእኛ ፈረስ ሊሆን ይቅርና እኛም የእርሱ ፈረሶች አይደለንም:: ይህ መዝሙር እየተቀናበረ እያለ በአጋጣሚ ስቱዲዮ ስለተገኘሁ ልክ አለመሆኑን ለዘማሪው ተናግሬ ነበር፤ የሰማኝ ባይኖርም:: ካሴቱ ግን ከነእንከኑ ታተመ:: አሁን ደግሞ ከዓመት በኋላ ይኸው መዝሙር ተነጥሎ በቪሲዲ ታትሞ ተሠራጨ:: መልእክታችን ጥሩ ቢሆን እንኳ የአገላለጽ ስሕተት የሚፈጠርበት አጋጣሚ ሊኖር እንደሚችል ያሳየናል::

«አጋንንቱም ጮኸ የእግዚአብሔር ልጅ ብሎ
እግሩ ሥር ተደፍቶ ይሉኝታውን ጥሎ» የሚለው ደግሞ የሰናይት እንግዳ #1 ካሴት ላይ ይገኛል:: ሰይጣን ይሉኝታውን ጥሎ በጌታ እግር ሥር ወድቆ ሲያመልክ ታያችሁ? እዚያ ሰፈር ያሉ ሰዎች በአቡነ ማንትስ አገልጋይነት ሰይጣን መነኮሰ የሚል ገድል አላቸው:: ይህን ነቅሶ

ለማውጣትና ለመሣለቅ ማን ብሎን? ይህስ መዝሙር ከዚህ በምን ተለየ? ወይስ ሌሎቹ ሲሉት ስሕተት የሆነው ነገር፣ እኛ ስንለው ትክክል ይሆናል?

«ጠላቴን አበሽቀዋለሁ» የሚል መዝሙርም ሰምተናል:: ዘማሪው ሳሙኤል ተገኝ ሲሆን፣ «ሰላምን ይሰጠናል» የሚል ኮሌክሽን ካሴት ነው:: ከሰይጣን ጋር ብሽሽቅና እንካ ሰላንትያ እንደ ተጀመረ እስካሁን ባለመስማቴ እኔም «በሽቁያለሁ»::

መዝሙር ትልቅ ጉልበት እንዳለው አልጠፋኝም:: መዝሙር በመስማት ብቻ ወደ ጌታ የመጡ ሰዎችን ዐውቃለሁ:: እኔም በተለያዩ ጊዜያት በመዝሙር ተባርኬያለሁ፤ ተጽናንቻለሁ፤ ተመልሼያለሁ:: አሁን እየታየ ያለው መረን የለቀቀና ዕውቀት የጐደለው አካሄድ ግን የአገልግሎቱን ክብር እንዳያጠፋው ያሰጋል:: «የአገልግሎቱ ክብር እንዲመለስ ከጠቀመ፣ እኔ መዘመሬን ዛሬውኑ ባቆም ደስተኛ ነኝ» ብሎኛል በዛሬው ጽሑፌ ከተቸኋቸው ዘማሪዎች አንዱ::

በዕዝራ የሥነ ጽሑፍ አገልግሎት የተዘጋጀና «ዘማሪዎቻችን» የሚል ሲዲ ባለፈው ሰሞን አግኝቼ ነበር:: ይህ ሰው ስለ ዘማሪዎች ችግር ዳሰሳ አድርጐ ስሕተቶችን ነቅሶ በማውጣት በሳል ትምህርትና ምክር አቅርቧል:: ጥሩ ዝግጅት እንደተደረገበት ያስታውቃል:: አንዱን ብቻ ልጥቀስ::

በርካታ ሰዎች የማያውቁትን ቃል መዝሙራቸው መሐል መሳግ ይወዳሉ:: ከእነዚህ ቃላት መሐል አንዱ «ጸባኦት» የሚለው ቃል ነው:: ጸባኦት፣ «በዕብራይስጥ ቋንቋ ሠራዊት፣ ጭፍራ ማለት ነው» ይላል የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኀበር ያሳተመው የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት:: ብዙዎች ግን፣ «የእግዚአብሔር ማደሪያ (ዙፋን)» የሚል ትርጉም እንዳለው ያስባሉ:: ይህንን ስሕተት የተሳሳቱት ብዙ ናቸው:: የቅርብ ጊዜ በመሆኑ የፓስተር ዳዊትን ከመጀመሪያ ካሴቱ ላይ ልጥቀስ
«ፈልጐት እኮ ነው አይደለም በከንቱ
አምልኮ ምስጋናው ገብቷል ጸባኦቱ»::

የማያውቁትን ቃል መጠቀም የሚያስገኘው የማናውቀው ጥቅም ሳይኖር የሚቀር አይመስለኝም:: እዚህ የፓስተር ዳዊት ሞላልኝ ካሴት ላይ፣ «ካቦድ ነው ዘንድሮስ ካቦድ ነው» የሚል መዝሙር ይገኛል:: ይህንን «ካቦድ» የሚል የአማርኛ ያልሆነና በመጽሐፍ ቅዱስም ላይ የሌለ ቃል በአማርኛ መዝሙር ውስጥ መገድገድ ምን ማለት ነው? ከትንሽ ጊዜ በኋላ እንደ ስብከቶቻችን ሁሉ በየጣልቃው የእንግሊዝኛ ቃላት የተገጠገጡባቸው አማርኛ መዝሙሮች እንደማንሰማ ዋስትና መስጠት የሚችል ሰው ይኖራል? ከሌሎቹ ለይቼ ፓስተር ዳዊትን መጥቀሴ ካሴቱ የቅርብ ጊዜ በመሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ «ፓስተር» ነውና መጽሐፍ ቅዱስን ከሌሎቹ በተሻለ ማወቅ እንደሚጠበቅበት ለማስገንዘብ ነው:: ግን ታዲያ በአክብሮት መሆኑን አትዘንጉብኝ::

የባዕድ ቃል ከመጠቀም በፊት የሚዘምሩበትን አገርኛ ቋንቋ ማዳበር ቀዳማይ ተግባር ቢሆን ይሻላል:: አሊያ፣ «አባቱ አያውቅ፤ አያቱን ይናፍቃል» ይሆንብናል:: ይህን የምለው የሚዘምሩበትን ቋንቋ ያለማወቅ ችግር እየታየ በመሆኑ ነው፤ ለምሳሌ የብዜት ችግር:: አማርኛ ቋንቋ የአማርኛ ብዜትና የግዕዝ ብዜትን ቀላቅሏል:: ሆኖም ከሁለቱ አንድን መርጦ እንጂ ሁለቱንም ቀይጦ መጠቀም ጸያፍ ነው:: መዝሙሮች ውስጥ ግን እንዲህ ዐይነቱ ችግር ተዘውትሮ ይታያል ::

ለምሳሌ ቃሎች ወይም ቃላት ማለት ሲኖርባቸው ቃላቶች ይላሉ:: መባል ግን የለበትም:: ኃያሎች ወይም ኀያላን ማለት ሲኖርባቸው ኀያላኖች፣ በንጉሥችና በነገሥታት ምትክ ነገሥታቶች፣ ነቢዮች፣ ወይም ነቢያት ለማለት ነቢያቶች፣ ኮከቦች ወይም ከዋክብት በማለት ፈንታ ከዋክብቶች መጽሐፎች ወይም መጻሕፍት ለማለት መጻሕፍቶች፣ በጸሐፊዎች ወይም ጸሐፍት ምትክ ጸሐፍቶች፣ ፈሪሳዊዎች ወይም ፈሪሳውያን ማለት ሲገባቸው ፈሪሳውያን ይላሉ:: ሁሉም ስሕተት ነው:: ስሕተቱ የእኛ ሰዎች ብቻ ሳይሆን፣ ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ያሉ ደራሲያንም ጭምር ነው:: ይህችን ቀላል የምትመስል ስሕተት ግን ግጥማኛቸውን አስቀድመው ቢያሳዩ (ቢያስገመግሙ) በቀላሉ ሊያስወግድት ይችላሉ::

አንድ ጊዜ አንዱ «ዓለማዊ» ሰው አንዱን ዘማሪ «እናንተ አካባቢ የውርስ ችግር አለ ወይ?» ብሎ ይጠይቀዋል:: «ምን ማለት ፈልገህ ነው?» ብሎ ይጠይቃል ይህኛውም:: «ማለቴ፣ እናንተ ጴንጤዎች መካከል ውርስን የሚመለከት ችግር ያለ መስሎኝ ነው» ይላል መልሶ:: «ለምን እንዲህ ልትል ቻልክ?» የእኛው ሰው ጠየቀ:: «መዝሙራችሁን ስሰማ፣ እያንዳንዱ ካሴት ላይ፣ አውርሶኝ ወርሼ፤ ልወርስ ስል፤ አትወርስም ብሎኝ ጠላቴ ምናምን አይጠፋውም:: መቼም የውርስ ችግር ባይኖርባቸው እንዲህ አይዘምሩም? ብዬ ነው» ነበር መልሱ::

መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት ከአንካሳ መረዳት ያስጥላል:: ስለ ክርስትና ያላቸውንም ሽውራራ መረዳት ያስተካክልላቸዋል:: አንድ ጊዜ አንድ የሶሪያ ንጉሥ ስለ እስራኤል አምላክ ሲናገር፣ «የተራራ አምላክ ነው» ብሎ ነበር (1ነገ. 21:23):: እኔ ደግሞ የዘማሪዎች አምላክም «የተራራ አምላክ» ይመስለኛል:: ቅጥ ያጣ ድለኝነት ያጠቃቸዋል:: ሁሌ ተራራና ከፍታ ብቻ ነው የሚታያቸው:: «ከፍታ የኔ የኔ! እኔስ ከፍታ (ድል) ነው የሚታየኝ፤ ከፍታ ከፍታ፤ የከፍታ ያለህ!» ማለት ይወዳሉ:: መቼም በሕይወት ሽለቆና ዝቅታ፣ በመከራና በስደት፣ በመገፋትም እያለፉ ያሉ ወገኖች የዚህን ዘመን ተመጻዳቂ መዝሙሮች ሰምተው ይጽናናሉ ብሎ ተስፋ ማድረግ የዋህነት ይሆናል:: ባይሆን እግዚአብሔር ለዘማሪዎቹ «እንደሚያዳላላቸው» ለመረዳት ያግዝ እንደሆን እንጂ!

ለዘማሪዎች ሁሌ ፋሲካ ነው:: ለነገሩማ፣ «በእውነትም በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ» ብቻ ናቸው የሚሰደዱት (2ጢሞ. 3:12):: «መዘበቻ በመሆንና በመገረፍ፣ ከዚህም በላይ በእስራትና በወህኒ» የተፈተኑ፣ በድንጋይ ተወግረው የሞቱ፣ በመጋዝ የተሠነጠቁ፣ በሰይፍ ተገድለው የሞቱ፣ ሁሉን እያጡ መከራን እየተቀበሉ፣ እየተጨነቁና የበግና የፍየል ሌጦ ለብሰው የዞሩ ዓለም ያልተገባቸውና በምድረ በዳና በተራራ በዋሻና በምድር ጉድጓድ የተቅበዘበዙ የእምነት አባቶች ነበሩን:: አሁንም አሉን:: ወደፊትም ይኖራሉ (ዕብ. 11:36-38):: ታዲያ ይህ ዋነኛ የወንጌል ክፍል ተዘልሎ ሁሌ ተራራና እንጀራ መዘመር ምን ይባላል? «የጅብ ቲዎሎጂ» ብሏል አንድ ወዳጄ::

ከዚህ ጋር አያይዤ የማነሣው ማኅበራዊ ፋይዳ ያላቸው መዝሙሮችን ለምን እንደማንዘምር ነው:: በቋንቋና በዘር መከፋፈላችን መዝሙር አይወጣው ይሆን? በኢትዮጵያ የዝማሬ ሰማይ ላይ ከሁሉም ይልቅ በድምቀት እያበራ ያለው ደረጀ ከበደ ባሕር ማዶ ሆኖ ይህንን መዘመር ከቻለ፣ እዚህ መሐል ያሉት አፋቸውን ምን ያዘው? ሥራ ፈትነት እና ስንፍናችንን፣ ስለ ኤች አይ ቪ ኤድስ መስፋፋት፣ ስለ ጉርፍና ስለ ሌሎች የተፈጥሮ አደጋዎች መዘመር ማንን ገደለ? የግድ ዘፋኞችን መጠበቅ አለብን እንዴ? በዚህ ውስጥ መልእክት ማስተላለፍ አይቻል ይሆን?

ብዙ ብዙ ነገሮችን መዘመር ይቻላል:: መቼም በዚህች ታሪከኛ አገር እየኖርን የአሳብ እጥረት አጋጠመን ቢባል ያስቀኛል:: እንደ ልብ የተተረፈረፈው ነገር ምን ሆነና?

«መዝሙር ጸጋ ነው ወይስ ተሰጥኦ?» የሚል አከራካሪ አሳብ መነሣቱ ባይቀርም ክፍት የሥራ ቦታ መሆኑን አንክድም:: ስለዚህ ወንጌላውያን፣ ፓስተሮች፣ ነጋዴው፣ ቦክሰኛውና ግምበኛው ሁሉ ዘማሪ ለመሆን ግፊያ ላይ ናቸው:: ሐዋርያው ያዕቆብም፣ «ደስ የሚለው ማንም ቢኖር እርሱ ይዘምር» ብሏልና ደስ ያለው ሁሉም መዘመር መብቱ ነው:: (ያዕ. 5:13):: ስለዚህ ብዙዎቻችን ስንጸልይ የምንጠቀምባቸው መዝሙሮች ሊኖሩን ይችላሉ:: «ደስ የሚለው ... ይዘምር» ማለት ግን፣ ካሴት ያውጣ ማለት ነውን? በጉባኤና በካሴት በመዝሙር ለማገልገል ተሰጥኦን ይጠይቃል:: የፈጠራ ችሎታንና አስተዋይነትን ይፈልጋል:: ረጋ ማለትና መስከን ግድ ነው:: ትንፋሽን ሰብስቦ ጊዜ መውሰድም ያስፈልጋል:: ዛሬ ዛሬ ሰነፍ ሴት የሠራችውን ያልበሰለና አረፋውን ያልከተተ ሽሮ በሚመስሉ መዝሙሮች የተጥለቀለቅንበት ምክንያትም ይኸው ይመስለኛል::

መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ የፈጠራ ችሎታን ይጨምራል እንጂ አይከለክልም:: ጥቂት ምሳሌዎችን ላክል:: «በዚያም ቀን ሰይፍ ከዋጠው ይልቅ ዱር ብዙ ዋጠ» (2ሳሙ. 18:18):: ይህንን ጥቅስ መጋቢ ተስፋዬ ጋቢሶ
«ሰይፍ ከዋጠው የበለጠ
የኀጢአት ዱር ብዙ ዋጠ» በማለት ዱሩ የኀጢአት መሆኑን ገልጾታል:: ድንቅ ፈጠራ ነው::

በትክክል በልካቸው የተሰፋ ዜማ ከነበራቸው ዘማሪዎች መሐል ታደሰ እሸቴ አንዱ ነበር፡፡ ከቁጥር 2 ካሴቱ ላይ አንድ መዝሙር ልጥቀስ፤
«ሃና መካኗ ሴት ብዙ አለቀሰች
በወገኖች ሳይቀር እየተነቀፈች»፡፡ ሃና ስትጸልይ ካህኑ ኤሊ ባለማወቅ ምን እንዳላት እናውቃለን (1ሳሙ. 14:17)፡፡ ታዴ ግን፣ ኤሊን በስም ከመጥቀስ ይልቅ «ወገኖች» ማለትን መርጧል፡፡ ስለዚህ በወገኖች የሚነቀፉ ወገኖች በመዝሙሩ ሊጽናኑ ይችላሉ፡፡ «ኤሊ» ብሎ ቢዘምር ኖሮ ውበቱና መልእክቱ ይደበዝዝ ነበር፡፡ «ሜልኮል» በማለት የሌለችን ሴት ስም እየጠሩ የሚያሰለቹን ሌሎች ዘማሪዎች ከዚህ ቢማሩ ደስ ይለኛል፡፡

ገዛኸኝ ሙሴ ደግሞ፣
«'ካልባረክሁህ አለልቅህም' የምትለኝ ይመስለኛል
አሊያማ ይህ ምሕረትህ መች ይገባኛል» ብሎ በቁጥር 3 ካሴቱ ላይ ዘምሯል፡፡ «ካልባረክኸኝ አልለቅህም» ብሎ የተናገረው ያዕቆብ ነበር (ዘዳ. 32:26)፡፡ እዚህ ጋ ግን፣ «ካልባረክሁህ አልለቅህም» የሚለው ጌታ ሆኖ ቀርቧል፡፡ ትክክለኛና ድንቅ ምልከታ ወይም ፈጠራ ሊባል ይችላል፡፡ ይገርማል! እግዚአብሔር፣ «የነገርሁህን እስካደርግልህ ድረስ አልተውህም» (ዘፍ. 28:15) በማለት ባይወስን ኖሮ ከዚህ አታካች ሰው ጋር ምን አደከመው?

ከዚህ ሁሉ ነጻ ለመውጣት መፍትሔው ብዙም አስቸጋሪ አይደለም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን (በተለያዩ ትርጉሞችና ማጥኒያዎች) ማጥናት፣ የተሻለና ብዙ የተለፋበት ሥራ የማቅረብ ቁርጠኛነት፣ የፈጠራ ችሎታቸውን ለማሻሻል የሚጠቅሙአቸውን ሥልጠናዎች መከታተል ወሳኝ ተግባራት ናቸው፡፡ መዝሙሮቻቸውን (በተለይ ግጥማቸውን) በተለያዩ ባለሙያዎች አስቀድመው ማሳየት፣ ዘፈን የሚሰሙባቸውን አጋጣሚዎች መቀነስ፣ ለጸሎት ጊዜ መመደብ፣ ድምፃቸውን ለማሻሻል ልምምድና ሥልጠና መውሰድ እንዲሁም ከሙዚቃ መሳሪያዎች ቢያንስ አንዱን ለመማር እንቅስቃሴ ቢያደርጉ አብዝተው ይጠቀማሉ፡፡ ሌላው ዕዳው ገብስ ነው፡፡ እግዚአብሔር ይርዳቸው፡፡

መጽሐፍ ቅዱስን መጠቀም ከፈጠራ እንደማያቅብ ትልቁ ምስክራችን ከዝማሬ ጡብ የተገነባ የሚመስለው ደረጀ ከበደ ነው፡፡ ናቡከደነጾርን «አውሬ ሆኖ አሳቡ» ይልና «ሲያመነዥግ ኖረ» ይለዋል፡፡ ስለ ኢትዮጵያ ሲዘምር፣ ኀፍረተ ሥጋዋ ባክኖ፣ እያነከሰችና እያለቀሰች ያለች ሴት በዜማ ይስልልናል፡፡ የሚጠቀምባቸው ቃላት ገጣሚነቱን ቁልጭ አድርገው ያሳያሉ፡፡ «ኀፍረተ ሥጋ፣ እትብት፣ ሽንጤን ገትሬ፣ የወሬ እርጐ፣ የሀሜት መረሬ፣ ምላሰ ረጅሙ፣ ቆንጥር፣ መርዶ፣ በዕንባ የራሰ ስሞታ፣ ላቦራቶሪ፣ ቁጥርን ከቁጥር ጋር ሲያጋጩ» እነዚህ እውን የዝማሬ ቃላትና ሐረጋት ይመስላሉ? ደረጀ ግን ለዝማሬ አውሏቸዋል፡፡ እግዚአብሔርን ሲፈልግ «ከልካይ» ብሎ ይጠራዋል፤ የእግዚአብሔርን መጠለያነት ደግሞ ከ«ዋርካ ጥላ» ጋር ያመሳስለዋል፡፡ ደረጀ ደፋር (በዕውቀት የሚደፍር) ነው፡፡ ዛሬም ከነገድና ከጐሳ ተዋጅተው ሳለ በጐሳና በዘር መቧደን ሙያ የሚመስላቸውን «ክርስቲያኖች» «ደጎንነት ሐሰት ነው የዘር ቀንበር ሳይወርድ» ብሎ እቅጯን እውነት ዘምሮላቸዋል፡፡ ደረጀ ለራሱ ታማኝም ነው፡፡ የፈጠራ ችሎታው ሰማይ ደርሷል፡፡ በድምፅ አጠቃቀሙ ቁንጮ ነው፡፡ በሙዚቃ ችሎታውም ቀዳሚ ነው፡፡

ደረጀ ድካም እንዳለበት አይካድም፤ ንጉሡ ዳዊትም እንዲሁ፡፡ ሆኖም ዳዊት የነገሥታት መለኪያ የሆነውን ያህል ደረጀ (ዳግማዊ ዳዊት) ደግሞ የዘማሪ መለኪያ ነው፡፡ ዘማሪና ዝማሬ ምን መምሰል እንዳለበት እኛ ኢትዮጵያዊያን ግራ እንዳንጋባ እግዚአብሔር ደረጀ ከበደን ሰጠን፡፡ ስለዚህ ትክክለኛ ዘማሪ ምን እንደሚመስል ለመረዳት ደረጀ ከበደን መመልከት ብቻ ከብዙ ልፋት ያድናል፡፡ ደረጀ መዝሙር ነው፤ መዝሙርም ደረጀ - ቢያንስ ለእኔ!

በእርግጥ ማንም ደረጀን መሆን አይችልም፤ እንዲሆንም አይጠበቅበትም፡፡ እንዲመስልም አንፈልግም፡፡ እያንዳንዱ ሰው የራሱ ቀለም አለውና ራሱን የሚሆን ሰው ነው የሚያስፈልገን! ሆኖም ከደረጀ ከበደ መማር መቻል ጠቢብነት ነው!